# Asylum Support Partnership
# help and advice

March 2012 Amharic

# ምንም ገቢ የሌልዎት እና የጥገኝነት ማመልከቻዎ ሂደት በመጨረሻ ደረጃ የደረሰ ጥገኝነት ፈላጊ ነዎትን?

ያቀረቡት የጥነኝነት ጥያቄ በየእንግሊዝ አገር የድንበር ኤጀንሲ (UK Border Agency - UKBA) ተቀባይነት አላገኘም ወይ? ያቀረቡት የጥገኝነት ጥያቄ አስመልክቶ ያገቡት የይግባኝ ጥያቄ ተቀባይነት አላገኘም? ከመንግስት በሚሰጠው እገዛ የሚተዳደሩ ከነበሩ - የእንግሊዝ አገር የድንበር ማህበር (UKBA) - UKBA እገዛ መስጠት አቋርጦ ይሆናል። ጥገኝነት ጠያቂዎች የይግባኝ መብታቸው ተጠቅመው ከጨረሱ ወዲህ፡ እነዚህ ሰዎች በ UKBA ማህበር የቀድሞ ጥገኝነት ጠያቂዎች ተብለው ይጠራሉ።

በተለምዶ ባለሥልጣናቱ እርስዎ በፈቃደኝነት እንግሊዝን  ለቀው እንዲወጡ ይፈልጋሉ፡ ወይም እርስዎን ለማባረር አስፈላጊውን ዝግጅት ያደርጋሉ። የ UKBA ማህበር እርስዎን ወድያውኑ ከእንግሊዝ አገር ለማባረር ካልቻለ፡ በማህል ባለው ጊዜ ውስጥ የመኖርያ ቤትና የገንዘብ እገዛ የሚሰጥዎት ክፍል አይኖርም።

ጉዳዩ እንደዚህ ከሆነ፡ ከሴክሽን 4 እገዛ (Section 4 support) በመባል የሚታወቀውን ልዩ የእገዛ ፕሮግራም እገዛ ለማግኘት ወደ UKBA ማህበር ማመልከቻ ማቅረብ ይገባል። ይህ እገዛ አብዛኛውን ጊዜ ልጅ ለሌላቸው የቀድሞ ጥገኝነት ፈላጊዎች የሚሰጥ እገዛ ነው። እድሜያቸው ከ 18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ያሏቸው ጥገኝነት ጠያቂዎች ግን እንግሊዝ አገርን ለቀው እስኪወጡ ድረስ እገዛው ይሰጣቸዋል።

## ይህ ሴክሽን 4 እገዛ የሚባለው ምንድን ነው?

ሴክሽን 4 እገዛ ለማግኘት አስፈላጊውን መስፈርት ያሟሉ ከሆነ፡ የ UKBA ማህበር የመኖርያ ቤት ከነእቃው እና ለምግብና ለመሰረታዊ የሽንት ቤት እቃዎች ለመግዛት የሚያስችልዎት የ 'Azure' ካርድ ይሰጥዎታል። ጥሬ ገንዘብ አይሰጥዎትም፤ የሚሰጥዎትን £35.39 በሰው በሳምንት ወደ  Azure የክፍያ ካርድዎ ላይ ይሞላል። ይህ የ Azure ካርድ በተወሰኑ ሱቆች ለምሳሌ በ Asda (አስዳ) እና Tesco (ቴስኮ) በመሳሰሉት መደብሮች መሰረታዊ የሆኑ ነገሮች እንደ ምግብ፣ የሽንት ቤትና የፅዳት እቃዎች ለመግዛት ይችላሉ። ስለ  Azure የክፍያ ካርድ የበለጠ መረጃ ከፈለጉ ወደሚከተለው ድረገጽ በመሄድ 'የ ሴክሽን 4 የ Azure የክፍያ ካርድ' በሚል አርእስት ላይ ለማንበብ ይችላሉ። http://languages.refugeecouncil.org.uk/english/summary.htm#26

እነዚህ የሚሰጡ የመኖርያ ቤት አገልግሎቶች ኣብዛኛው ጊዜ ከለንደን ከተማ ውጭ ናቸው። የሚቀርብሎት የመኖርያ ቤት እድል አንዴ ስለሆነ በሆነ ምክንያት የቀረበሎትን ቤት ለመውሰድ ፍቃደኛ ካልሆኑ፣ የ UKBA ማህበር የሚሰጥዎን ድጋፍ ሊያቋርጡት ይችላሉ። ነገር ግን፡ ልዩ በሆኑ ጉዳዩዎች፡ የሴክሽን 4 እገዛ የሚቀበሉ ጥገኝነት ፋላጊዎች ከዘመዳቸው አቅራቢያ በሆኑ ቦታዎች የመኖርያ ቤት ሊሰጣቸው ይችላል። ኣብዛኛው ጊዜ በነዚህ የመኖርያ ቤቶች ሲገቡ ከሌሎች ሰዎች ጋር በጋራ የመኖር እድሎ ከፍተኛ ነው። ሆኖም ግን፡ ከሌሎች ሰዎች አብሮ ለመኖር የማይችሉበት ልዩ የሆነ ምክንያት ካልዎት፡ እነዚህ ምክንያቶች ምን እንደሆኑ በዝርዝር በመግለጽ በጽሁፍ ለ UKBA ማህበር ጉዳይዎን ማቅረብ አለቦት፡፡

## የሴክሽን 4 እገዛ ለማግኘት ብቁ የሚያደርጉ መስፍርቶች ምንድን ናቸው?

የ UKBA ማህበር ማን የሴክሽን 4 እገዛ ማግኘት እንደሚችል የሚወሥንበት ጥብቅ የሆኑ መስፍርቶች አሉት። ከመስፈርቶቹ  እንዱ  ምንም ገቢ የሌልዎት ወይም በ 14 ቀናት ውስጥ ገቢዎ የሚቋረጥ መሆኑ ነው፤ ይህ ማለት ደግሞ ምንም አይነት የመኖርያ ቤት እና/ወይም ምግብ ለእርሶ ወይም በስርዎ ላሉት ሰዎች እንደሌሎት እና ይህንንም ማሟላት የሚችሉበት መንገድ እንደሌለ እና መደበኛ ፍላጎቶቻችሁን ማሟላት አይችሉም ማለት ነው። በተጨማሪም እስከ አሁን እንዴት ራስዎን ያስተዳድሩ እንደነበር፤ ለሚያቀርቧቸው ምክንያቶች ደግሞ ማስራጃዎች ማቅረብ ይገባል።


Asylum Support Partnership is a partnership project hosted by the British Refugee Council
British Refugee Council, (commonly called the Refugee Council) is a company limited by guarantee registered in England and Wales, [No 2727514] and a registered charity, [No 1014576].

በተጨማሪም ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ቅድመ ሁኔታዎች ቢያንስ **አንዱን** የሚያሟሉ መሆንዎን ማሳየት አለብዎት፤

1. እንግሊዝ አገርን ለቀው የመውጣት ዝግጅት እያደርጉ መሆነዎን ማሳየት ወይም ራስዎ የመጀመርያ እርምጃ እያሳዩ መሆንዎን ማሳየት ይገባል።
2. ወይም ባልዎት የጤንነት ችግሮች ለምሳሌ ህመሞች ወይም ለመውለድ ትንሽ ቀን የቀርዎት እርጉዝ እናት በመሆንዎ እንግሊዝን ለቀው መውጣት እንደማይችሉ ማሳየት
3. ወይም፡ በ UKBA ማህበር ለጥገኝነት ማመልከቻው የሰጠውን ውሳኔ ለመከራከር ይግባኝ እንዳሉና ጉዳይዎ ደግሞ ወደ ከፍተኛ ፍርድ ቤት (High Court) እንደተላለፈ ማሳየት፡ ማስታወስ ያለብዎት ነገር በስኮትላድ ላይ ከሆኑ ጉዳይዎ በህግ እንደገና ሊታይ እንዳመለከቱ የሚያሳይ ማረጋገጫ ካቀረቡ በቂ ነው። ወይም ደግሞ በ UKBA ማህበር ላይ አዲስ ያልተፈታ የጥገኝነት ጥያቄ ሊኖርብዎት ይችላል
4. ወይም ወደ አገርዎ ለመመለስ ሰላም የሆነ መንገድ የሌለ መሆኑን ካሳዩ። በ UKBA ማህበር አመለካከት ደግሞ፡
በአሁኑ ጊዜ ይህን ችግር ያለበት አገር የለም። ይህ ከተለወጠ ደግሞ የህግ አማካሪዎ ወይም የዋንስ ስቶፕ አገልግሎት (One Stop Service) አማካሪዎ ሊነግርዎት ይችላል
5. ወይም የመኖርያ ቤት ካልተሰጥዎት ሰብኣዊ መብትዎን መጣስ መሆኑን ካሳዩ። ለምሳሌ፡ አዲስ የጥገኝነት ማመልከቻ ካስገቡና በዚህ ማመልከቻ ያለው መረጃ አስቀድመው ካቀረቡት የተለየ ከሆነ፡ የሴክሽን 4 እገዛ ማግኘት ይገባል።

የ UKBA ማህበር ለሴክሽን 4 እገዛ ለሚያመለክቱ ሰዎች የእያንዳንዱ አመልካች መልካም ስራን ይመለከታል፡ እንዲሁም ወደ አገርዎ ለምን ለመመለስ እንዳልቻሉና ለምን ለመጓዝ እንደማይችሉ ያልዎትን ምክንያዎቶች የሚያሳዩ ማስረጃዎች እንዲያቀርቡ ይጠይቃል። እነዚህ ማስረጃዎች ደግሞ፡ እርስዎ ለመጓዝ እንደማይችሉ የሚገልፁ የዶክተር ወረቀት ወይም ከከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳይዎን በተመለከተ ቀጠሮ እንዳልዎት የሚሳይ ደብዳቤ የመሳሰሉትን ማስረጃዎች ያጠቃልላል።

## የሴክሽን 4 እገዛ ለማግኘት እንዴት ለማመልከት ይቻላል?

ለዚህ የሴክሽን 4 እገዛ ለማመልከት የሚፈጉ ጥገኝነት ፈላጊዎች የሚሞሉት ሁለት ቅጾች ይገኛሉ። የሴክሽን 4 እገዛ ማመከቻ ፎርም ከፈለጉ ቀጥሎ ባለው ድረገጽ ሊያገኙ ይችላሉ http://www.ukba.homeoffice.gov.uk/asylum/support/apply/section4/ በአከባቢዎ የሚገኘው የዋንስቶፕ አገልግሎትን ማነጋገር ይችላሉ፡ የትኛው ቅጽ መሙላት እንዳለብዎትና እንዴት ለመሙላት እንደሚችሉ ምክር በመስጠት እርዳታ ያቀርብሎታል። የዋንስቶፕ አግልግሎት የተሞላውን ማመልከቻዎ ወደ UKBA ማህበር እንዲመለከቱት በመላክ ለሚገኘው ውሳኔ ያሳውቆታል፤ በተጨማሪም ስለ ሌሎች እገዛዎች መረጃ ይሰጥዎታል፤ ለምሳሌ፡ ከመኖርያ ቤትዎ ወደ ሪፓርት ማድረግያ ጣብያ የመጓጓዣ ወጪዎች፣ በአከባቢዎ የሚገኝ የዋንስቶፕ አገልግሎት አድራሻ ለማግኘት የበለጠ መረጃ በዚህ አጭር ጽሁፍ መጨረሻ ላይ ይገኛል።

ከዋንስቶፕ አገልግሎት በስተቀር፡ የሴክሽን 4 እገዛ ማመልከቻ ለማድረግ የህግ አማካሪዎ፡ የአከባቢ የህግ ማእከል፡
የዜጎች ምክር (Citizens Advice) ወይም የስደተኛ ማህበሮች የመሳሳሉት አካሎች ሊተባበርዎት ይችላሉ።

ያገኙት የነበረውን እገዛ እንደሚቋረጥ የሚገልጽ ደብዳቤ ከ UKBA ማህበር ከተቀበሉ በኋላ እባክዎን ወድያውኑ ለሴክሽን 4 እገዛ ማመልከት እንደሚገባዎት ያስተውሉ

የሴክሽን 4 እገዛ ለማግኘት ከደንቦችና ቅድመ ሁኔታዎች ጋር መስማማታቸውን ለመግለጽ፡ የማመልከቻ ፎርሙ ላይ መፈረም ይገባል።

- የሴክሽን 4 እገዛ መሰረታዊ የሆነ የመኖርያ ቤትን ያካትታል።
- አብዛኛው ጊዜ የ UKBA ማህበር ከለንደን ከተማ ውጭ የመኖርያ ቤት ያቀርባል፡ ይህ ማለት ደግሞ እርስዎ ለንደን ከተማ የመኖርያ ቤት ሊያሰጥዎት የሚችል ልዩ የሆነ ምክንያት ከሌልዎት በስተቀር በለንደን ከተማ ውስጥ የመኖያ ቤት አይሰጥዎትም
- ሁሉንም የፋይናንስ መረጃ ለማቅረብ ተስማምተዋል እና UKBA ዳታውን እንዲያገኝ ፈቃድ ሰጥተዋል እንዲሁም በሌሎች ኤጀንሲዎች ማለትም የፋይናንስ ዳታን ጨምሮ ይህም ደግሞ ሊያገኙ የሚገባውን ለመፈተሽ እና የተጭበረበረውን ለመቀነስ ይረዳው ዘንድ ለመስጠት ተስማምተዋል፡፡
- ዘገባን እና ለመረጃ የሚሆኑ ተጨማሪ ጥያቄዎችን ጨምሮ እገዛው በሚሰጥበት ስር ያሉ ማንኛውን ሁኔታዎች ማሟላት የሚሳንዎ ከሆነ፣ ሊወጣ ይችላል፡፡
- የሴክሽን 4 እገዛ የሚቀበሉ ከሆነና ባለሥልጣናቱ መረጃ እንዲሰጡ በሚጠይቅዎት ጊዜ፡ የተጠየቀውን መረጃ ማቅረብ ይገባል።

ያቀረቡት ማመልከቻ ተቀባይነት ካገኘ፡ የ UKBA ማህበር በታቸለ መጠን በጥቂት ቀኖች ውስጥ የመኖርያ ቤት ያገኙሎታል። በተጨማሪም ወደ መኖርያ ቤቱ እንዲሄዱ የጉዞ ቲኬት ይልክሎታል።

## የሴክሽን 4 እገዛ ለስንት ጊዜ ያህል ለማግኘት እችላለሁኝ?

የሴክሽን 4 እገዛ ለማግኘት መስፈርት እንዳሟሉ የ UKBA ማህበር በየጊዜው ግምገማ ያደርጋል። ይህ ሲባል ደግሞ የነበርዎትን ሁኔታ ከተቀየረ ወይም እንግሊዝ አገር ለቀው ለመውጣት የሚገታዎት ችግሮች ያሉ እንደሆነ ያረጋግጣሉ ማለት ነው።

## የሴክሽን 4 እገዛ ለማግኘት ያቀረብኩት ማመልከቻ ተቀባይነ ካጣ ምን ይሆናል?

የ UKBA ማህበር የሴክሽን 4 እገዛ ለማግኘት የማይፈቅድ ከሆነ፡ የተሰጠው ውሳኔን በመቃወም ይግባኝ ለማለት ይችላሉ፡ ይግባኝ ለማለት ደግሞ የዋን ስቶፕ አገልግሎት ጽህፈት ቤት ሊተባበርዎት ይችላል። በጣም አጭር በሆነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ማመልከት ያስፈልግዎታል - ብዙውን ጊዜ የ UKBA የውሳኔ ደብዳቤ በአምስት ቀናት ውስጥ፡፡

የሴክሽን 4 እገዛ ለማግኘት ካመለከቱ ወዲህ፡ ሁኔታዎ ከተቀየረ መልሰው ሌላ ማመልከቻ ማስገባት ይገባል። የጥገኝነት ጥያቄዎን በተመለከተ አዲስ ማስረጃ ከተገኘ፡ እንደገና ማመልከቻ ማቅረብ ይችላሉ። የ UKBA ማህበር እርስዎ በእርግጥ ምንም ገቢ የሌልዎት መሆንዎን በማረጋገጥ፡ ካደረጉት የመጨረሻ ማመልከቻ ወዲህ የነበረውን ጊዜ እንዴት ሊኖሩ እንደቻሉ ይጠይቅዎታል።

## ምን አይነት ሌሎች እገዛዎች አሉ?

የአካል ስንክልና ወይም የመማር፡ የመስማት ወይም የማየት ችግር፡ የአእምሮ ወይም ሌላ የማይድን ህመም ካለብዎት፡ አከባቢዎ የሚገኘው የአከባቢ ባለሥልጣን የማህበራዊ አገልግለቶች (social services) ክፍል በመሄድ መጠየቅ አለብዎ። እርስዎ ወይም በእርስዎ ምትክ ሌላ እርሶን የሚወክል ሰው ወደ አከባቢ ባለሥልጣን የማህበራዊ አገልግለቶች ክፍል በመሄድ ስለ የኮሚኒቲ እንክባካቤ ፍላጎት ግምገማ እንዲደረግ መጠየቅ አለብዎ።

የጥገኝነት ጥያቄዎን በተመለከተ የመጨረሻ ይግባኝ መብትዎን ተጠቅመው ማመልከቻ አስገብተው መልስ እየጠበቁና የሴክሽን 4 እገዛ ከማግኘት የተከለከሉ ከሆነ፡ ከበጎ አድራጊ ማህበሮች እርዳታ መጠየቅ ይችላሉ። በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ፡ አንዳንድ የአከባቢ የኮሚኒቲ ማህበሮች እንደ ረፍዩጂ ኮሚኒቲ ወይም የእምነት ቡድን የመሳሰሉት ማህበሮች የሞቁ ምግቦች፡ የታሸጉ ምግቦች፡ የሽንት ቤት እቃዎች እና ልብሶች ያቀርባሉ።

የትኛው የበጎ አድራጊ ማህበር እነዚህ ነገሮች ሊሰጥዎት እንደሚችል ለማወቅ ከፈለጉ፡ አቅራብያዎ የሚገኝ የዋንስቶፕ አገልግሎት፡ የቀይ መስቀል (Red Cross) ጽህፈት ቤት፡ የዜጎች ምክር ወይም የአከባቢ የምክር ማእከል ለመጠየቅ ይችላሉ። ወይም በአከባቢው ቤተ መፅሀፍት በመሄድ የነዚህ ማህበሮች አድራሻ ለመጠየቅ ይችላሉ። የአከባቢው ባለሥልጣን ጽህፈት ቤት፡ በዚህ መንገድ ምንም ገቢ የሌላቸው ጥገኝነት ፈላጊዎች የሚሆን የተዘጋጀ የእርዳታ አገልግለቶች ሊኖራቸው ይችላል።

## ዋንስቶፕ አገልግለቶች

የሰሜን እንግሊዝ የስደተኞች አገልግሎት (North of England Refugee Service)፣ ረፍውጅ አክሽን (Refugee Action)፣ የረፍውጅ ካውንስል (Refugee Council)፣ ረፉውጅ ካውንስል በስኮትላንድ (Scottish Refugee Council) እና ረፉውጅ ካውንስል በዌልስ (Welsh Refugee Council) የመሳሰሉት የበጎ አድራጊ ማህበሮች ለጥገኝነት ፈላጊዎችና ስደተኞች እርዳታ ምክር የሚያቀርቡ ዋናዋና ማህበሮች ናቸው። እነዚህ የበጎ ኣድራጎት ማህበሮች ስለ መኖርያ ቤት፣ የመኖርያ ድጋፍ፣ ጥገኝነት፣ ጤና እና በመላው እንግሊዝ በሚገኙ የዋን ስቶፕ አገልግሎቶች በኩል የተለያዩ ምክሮችና እርዳታዎች ይሰጣሉ።

ቀጥሎ ያለውን ድረገጽ በመጎብኘት በአከባቢዎ የሚገኘውን የዋን ስቶፕ አገልግሎት አድራሻ ለማግኘት ይችላሉ፡ [http://languages.refugeecouncil.org.uk/english/services.htm](http://languages.refugeecouncil.org.uk/english/services.htm)

## በቁጥጥር ስር ውለዋል እና የዋስትና አድራሻ ያስፈልግዎታል

በቁጥጥር ስር የዋሉ ስደተኞች ውስጥ ከሆኑ እና የዋስትና ማመልከቻን ለማቅረብ የሚያመቻችልዎት ከፈለጉ በ UKBA ድረ ገጽ የሴክሽን 4 ድጋፍን የሴክሽን 4 የማመልከቻ ቅጽን (Section 4 Bail Application Form) በመጠቀም ማመልከት ይችላሉ፡ [http://www.ukba.homeoffice.gov.uk/sitecontent/applicationforms/asylum/section_4_bail_application_1.pdf](http://www.ukba.homeoffice.gov.uk/sitecontent/applicationforms/asylum/section_4_bail_application_1.pdf)

በቁጥጥር ስር ከዋሉ፣ ችግረኛ እንደሆኑ ማሳየት ለእርስዎ ጠቃሚ ነው ወይም ለሴክሽን 4 ድጋፍ ብቁ ይሆኑ ዘንድ ከላይ ከተገለጹትን አምስቱን የብቃት መስፈርት ማናቸውንም እንደሚያሟሉ ማሳየት ይጠቅምዎታል፡፡

በቁጥጥር ስር የዋሉትን ከሚጎበኙ ቡድኖች አንዱ ዋስ እንዲሆኖዎት እንዴት ማመልከት እንዳለብዎ ለማወቅ በሚከተለው ድረ ገጽ ተጨማሪ መረጃን ያገኛሉ፡http://www.aviddetention.org.uk/index.php?option=com_content&view=category&id=5&Itemid=5 ወይም በቁጥጥር ስር ከዋሉ ስደተኞች ዋስትና (Bail for Immigration Detainees) www.bid.org

Asylum Support Partnership consists of:

North of England Refugee Service, charity number: 1091200 www.refugee.org.uk
Refugee Action, charity number: 283660 www.refugee-action.org.uk
Refugee Council, charity number: 1014576 www.refugeecouncil.org.uk
Scottish Refugee Council, charity number: SC008639 www.scottishrefugeecouncil.org.uk
Welsh Refugee Council, charity number: 1102449 www.welshrefugeecouncil.org